በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገንዘብ ሚኒስቴር
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF FINANCE

ቁጥር Ref. No ማ/ኢ30/7/1791
ቀን Date 5/13/2013

ለገቢዎች ሚኒስቴር
ለጉምሩክ ኮሚሽን
<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡- <u>የጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ይመለከታል</u>፡፡

በጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ (ማሻሻያ) የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 153/2000 በአንቀጽ 3 ለገንዘብ ሚኒስቴር በተሰጠው የሥልጣን ውክልና መሠረት ሀምሌ 28 ቀን 2013 ዓ.ም በቁጥር ማኢ.30/7/1141 በተጻፈ ደብዳቤ የጉምሩክ ታሪፍ ማሻሻያ መደረጉ ይታወሳል፡፡

በዚህም ማሻሻያውን ተከትሎ መስተካከልና መናበብ ያለባቸው ጉዳዮች በመኖራቸው የሚከተለው ማስተካከያ ተደርጓል፡-

1. ከዚህ በፊት ለግብርና ሜካናይዜሽን በልዩ ሁኔታ መስከረም 12 ቀን 2012 ዓ.ም በቁጥር ማኢ.30/7/7፣ ጥቅምት 05 ቀን 2012 ዓ.ም በቁጥር ማኢ.30/6/41 እና መጋቢት 25 ቀን 2012 ዓ.ም በቁጥር ማኢ.30/7/45 የተላለፉ መመሪያዎች ተሠርዘው በሚከተለው ተተክተዋል፤

1.1. ከዚህ በታች በሠንጠረዥ 1 የቀረቡት እቃዎች፣ መሣሪያዎች እና ግብዓቶች ለግብርና አገልግሎት የሚውሉ በመሆናቸው ከውጭ ሲመጡ ወይም በአገር ውስጥ ተመርተው ለግብርና ዓላማ ሲቀርቡ ከማንኛውም ቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲሆኑ፤

ሠንጠረዥ 1፡ ለግብርና ዓላማ ሲቀርቡ ከማናቸውም ቀረጥና ታክስ ነፃ የሆኑ

| ተ.ቁ | ታሪፍ ቁጥር | የዕቃው ዓይነት |
|---|---|---|
| 1 | 0102.2100 | በህይወት ያሉ የቀንድ ከብቶች የንፁህ ዘር ማራቢያ እንስሳት |
| 2 | 0104.1000 | በህይወት ያሉ በጎች (ለዘርያ ማሻሻያ) |



ስልክ 251-11-155 24 00,22 66 98 251-11-155 00 81,83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ P.O.Box 1905,1037 እባክዎን መልስ ሲፅፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ
ፋክስ/Fax 251-11-156 01 24,55 14 96 251-11-155 11 38
MoF_Ethiopia facebook.com/MoFEDet mofed.gov.et

ቁጥር
Ref. No
ቀን
Date.

| ተ.ቁ | ታሪፍ ቁጥር | የዕቃው ዓይነት |
|---|---|---|
| 3 | 0104.2000 | በህይወት ያሉ ፍየሎች (ለዝሪያ ማሻሻያ ለወተት ልማት) |
| 4 | 0105.9400 | የጋሉስ ዶመስቲከስ ዝርያ የሆኑ መሰረተ ርቢ ዶሮዎች፣ የጋሉስ ዶመስቲከስ ዝርያ የሆኑ የንጹህ መራቢያ ዶሮዎች፣ የጋሉስ ዶመስቲከስ ዝርያ የሆኑ መሰረተ ርቢ ዶሮዎች የአንድ ቀን ጫጩቶች |
| 5 | 0106.1300 | በህይወት ያሉ ግመሎች እና ካምሊዮድስ (ለወተት ልማት) |
| 6 | 0301.1100 | በሕይወት ያሉ ጌጠኛ ዓሣዎች ለርቢ |
| 7 | 0301.9900 | በሕይወት ያሉ ዓሣዎች ለርቢ |
| 8 | 0303.9900 | የለማ የዓሳ እንቁላል እና ሕይወት ያለው ዓሳ ለማራባት |
| 9 | 0407.1100 | የጋሉስ ዶመስቲከስ ዝርያ ዶሮዎች የሆኑ ለርቢ የሚሆኑ ለም እንቁላል |
| 10 | 0511.1000 | የቀንድ ከብት አባለዘር (ስሜን) |
| 11 | 0511.9900 | የሃር ትል እንቁላል |
| 12 | 2308.0000 | አትክልት እና የአትክልት ውዳቂ፣ ዝቃጮችና አንዳኝ ውጤቶች፣ የተድበለበለ የሆነም ያልሆነም፣ ለእንስሳት መኖ የሚውሉ ዝግጅቶች |
| 13 | 2309.9010 | የእንስሳት እና የድሮ መኖ ለማምረት የሚያገለግሉ ቀዳሚ ድብልቆች |
| 14 | 2309.9090 | የዓሣ እና ክርስታሽያንስ መኖዎች፣ ተጨማሪ ተንሳፋፊ የዓሣ መኖ |
| 15 | 2937.2300 | የዳልጋ ከብት ድራት ማጎልበቻ ሆርሞን |
| 16 | 2937.5000 | የዳልጋ ከብት ድራት ማጎልበቻ ሆርሞን |
| 17 | 5608.1100 | የተዘጋጁ የዓሣ ማጥመጃ መረቦች |
| 18 | 5608.9090 | በናይለን መልቲ ፊላሜንት የተሰሩ የዓሣ ማጥመጃ መረቦች |

1.2. በሠንጠረዥ 2 የቀረቡት ለግብርና የሚውሉ እቃዎች በመጡ ጊዜ ሁሉ በግብርና ሚኒስቴር ማረጋገጫ እየተሰጠባቸው ወደ አገር ሲገቡም ሆነ ለግብርና ዓላማ ከአገር ውስጥ ምርት ግብይት ሲፈጸምባቸው ከማንኛውም ቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲሆኑ፤



ስልክ
251-11-155 24 00,22 66 98
251-11-155 00 81,83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ
P.O.Box 1905,1037
አባክዎን መልስ ሲፅፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ
ፋክስ/Fax
251-11-156 01 24,55 14 96
251-11-155 11 38
MoF_Ethiopia
facebook.com/MoFEDet
mofed.gov.et

ቁጥር
Ref. No

ቀን
Date.

በዚህም በሠንጠረዥ 2 የቀረቡት ዝርዝሮች የሚስተናገዱት ከእያንዳንዱ ታሪፍ ቁጥር ጎን የተገለጸው የእቃው ዓይነት (ስም) እየተረጋገጠ ሲሆን፣ የእቃው ዓይነት በስሙ ያልተገለጸ እቃ ታሪፍ ቁጥሩ ቢቀመጥም እንኳን የማይስተናገድ ይሆናል።

**ሠንጠረዥ 2፡ በግብርና ሚኒስቴር ቁጥጥር እየተደረገባቸው ከማንኛውም ቀረጥና ታክስ ነፃ የሆኑ የግብርና ግብአቶች**

| ተ.ቁ | ታሪፍ ቁጥር | የዕቃው ዓይነት |
|---|---|---|
| 1 | 3917.3910 | ለመስኖ ውሃ ማስተላለፊያ አገልግሎት የሚውሉ የፕላስቲክ ቱቦዎች ዲያሜትራቸው ከ630 ሚሊ ሜትር በላይ የሆኑ ትቦዎች፣ ቧንቧዎች እና ሆዞች |
| 2 | 3917.4010 | ለመስኖ ውሃ ማስተላለፊያ አገልግሎት ከ630 ሚሊ ሜትር በላይ ለሆኑ ትቦዎች፣ ቧንቧዎች እና ሆዞች የሚውሉ ተገጣጣሚዎች |
| 3 | 5607.9000 | ናይለን መልቲ ፊላሜንት የዓሣ ማጥመጃ መረብ መስሪያ ድርብ ክር |
| 4 | 5608.1990 | የዓሣ ማጥመጃ ድርብ ክር |
| 5 | 7311.0000 | የፈሳሽ ናይትሮጅን ኮንቴይነር፣ የብረት ወይም አይረን |
| 6 | 7326.9090 | የአረብ ብረት የተቀባ የእናት ንብ ማግለያ |
| 7 | 8201.6000 | ቁጥቋጦ መከርከሚያ መቀሶች፤ ባለ ሁለት እጅ የእጽዋት መግረዣ መቀሶች፤ ከባለ ሁለት እጅ መቀስ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው መቀሶች |
| 8 | 8201.9090 | ሰም ማያያዣ ኢምቤደር |
| 9 | 8407.2100 | የዓሣ ማጥመጃ እና መሰብሰቢያ ጀልባ ሞተር (ከውጪ ጀልባ ላይ የሚገጠም) |
| 10 | 8413.1900 | ለመስኖ አገልግሎት የሚውሉ ፓምፖች |
| 11 | 8413.5000 | ወደፊትና ወደ ኋላ በሚንቀሳቀስ ዘንግ የሚሰሩ የመስኖ ፓምፖች በታዳሽ ሃይል የሚሰሩ |
| 12 | 8413.6000 | ተዘዋዋሪ የሆኑ የመስኖ ፓምፖች በታዳሽ ሃይል የሚሰሩ |
| 13 | 8413.7000 | በታዳሽ ሃይል የሚሰሩ ለመስኖ ውሀ መሳቢያነት የሚያገለግሉ ሴንትሪፉውጋል ፓምፖች |
| 14 | 8413.8100 | በታዳሽ ሃይል የሚሰሩ ለመስኖ የሚውሉ ፓምፖች |
| 15 | 8413.8200 | ለመስኖ ውሀ መሳቢያነት የሚያገለግሉ ፓምፖች፣ የውሃ መሳቢያ ፓምፖች በትራክትር ፒቲኦ የሚሰራ |



ስልክ
251-11-155 24 00,22 66 98
251-11-155 00 81,83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ
P.O.Box 1905,1037
እባክዎን መልስ ሲፅፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ
ፋክስ/Fax
251-11-156 01 24,55 14 96
251-11-155 11 38
MoF_Ethiopia
facebook.com/MoFEDet
mofed.gov.et

ቁጥር
Ref. No
ቀን
Date.

| ተ.ቁ | ታሪፍ ቁጥር | የዕቃው ዓይነት |
|---|---|---|
| 16 | 8413.9100 | ለመስኖ የሚውሉ የፓምፖች ክፍሎች |
| 17 | 8413.9200 | ለመስኖ ውሀ ወደ ከፍታ ለማውጣት የሚያገለግሉ የፓምፖ ክፍሎች |
| 18 | 8414.2000 | በእጅ ወይም በእግር የሚንቀሳቀሱ የአየር ፓምፖች (የመስኖ ውሃ ለማውጣት የሚያገለግሉ ትሬድል፣ ፔዳል፣ ሮፕ እና ወሸር የመሳሰሉ) |
| 19 | 8414.5900 | ለዓሣ ኩሬ ግብርና የዓሣ ጫጩት ማስፈልፈያ አየር መስጫ ኮምሬሰር፣ ፋን እና አይሬተር፣ የአኳካልቸር |
| 20 | 8414.9000 | ለመስኖ የሚውሉ በታሪፍ ቁጥር 8414.2000 ለተመደቡ ዕቃዎች ክፍሎች |
| 21 | 8419 8900 | በከፍተኛ ሙቀት ደረጃ የሚሰራ ምድጃ ጀርሞችን ለማፅዳት የሚያገለግል፣ የቆርቆሮ ዓሣ ጥቃቅን ህዋሳት ማምከኛ መሳሪያ፣ ጀንተር ህብረ-ንብ ርቢ ሙሉ ዕቃ፣ የጠብታ መስኖ ስርዓት እቃዎች፣ |
| 22 | 8421.1100 | ክሬም መለያ |
| 23 | 8421.1900 | የማር ማጣሪያ በተለያየ ፍሬም ቁጥር መጠን፣ በእጅ የሚሰራ፣ የዶሮ ኩስ እርጥበትን መስወገጃ ማሽን፣ የወተት ቅባት መለያ እና ሴንትሪፉጅ፣ |
| 24 | 8424.9000 | የግብርና መርጫዎች ክፍሎች፣ የርጭት መስኖ መለዋወጫዎች |
| 25 | 8432.9000 | ክፍሎች |
| 26 | 8433.9000 | ክፍሎች ሄደር ለሰብልና ለመኖ ማጨጃ / መሰብሰቢያ ጨምሮ |
| 27 | 8434.9000 | የወተት ማለቢያ ማሽኖች ክፍሎች |
| 28 | 8436.9900 | የዓሣ መኖ ማዘጋጃ ማሽነሪዎች ክፍሎች፣ ለንብ ዕርባታ የሚውሉ ማሽነሪዎች ክፍሎች |
| 29 | 8437.9000 | የ8437.1000 እና 8437.8000 ማሽኖች ክፍሎች፣ የኤማቶድ ናሙና መለያ ወንፊት፣ |
| 30 | 8501.3230 | ለመስኖ ውሃ ከጥልቅ ጉድጓድ ወይም ከወንዞች ወይም ከኩሬ ወይም ከግድብ ወደ ማሳ ለመግፋት የሃይል አማራጭ የሚውሉ ሃይላቸው ከ750 ዋት የበለጠ ነገር ግን ከ75 ኪዋት ያልበለጠ ለመስኖ የሚያገለግሉ ሞተሮች |
| 31 | 8501.3330 | ውሃ ከጥልቅ ጉድጓድ ወይም ከወንዞች ወይም ከኩሬ ወይም ከግድብ ወደማሳ ለመግፋት የሃይል አማራጭ ሃይላቸው ከ75 ኪ.ዋት የበለጠ ነገር ግን ከ375 ኪ.ዋት ያልበለጠ ለመስኖ የሚያገለግሉ ሞተሮች |
| 32 | 8501.3430 | ውሃ ከጥልቅ ጉድጓድ ወይም ከወንዞች ወይም ከኩሬ ወይም ከግድብ ወደማሳ ለመግፋት የሃይል አማራጭ ሃይላቸው ከ375 ኪ.ዋት የበለጠ ለመስኖ የሚያገለግሉ ሞተሮች |



ስልክ
251-11-155 24 00,22 66 98
251-11-155 00 81,83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ
P.O.Box 1905,1037
እባክዎን መልስ ሲፅፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ
ፋክስ/Fax
251-11-156 01 24,55 14 96
251-11-155 11 38
MoF_Ethiopia
facebook.com/MoFEDet
mofed.gov.et

ቁጥር
Ref. No
ቀን
Date.

| ተ.ቁ | ታሪፍ ቁጥር | የዕቃው ዓይነት |
|---|---|---|
| 33 | 8501.4030 | ውሃ ከጥልቅ ጉድጓድ ወይም ከዎንዞች ወይም ከኩሬ ወይም ከግድብ ወደማሳ ለመግፋት የሃይል አማራጭ፣ በነጠላ ፌዝ የሚሰሩ ኤሲ ሞተሮች |
| 34 | 8501.5230 | ውሃ ከጥልቅ ጉድጓድ ወይም ከዎንዞች ወይም ከኩሬ ወይም ከግድብ ወደማሳ ለመግፋት የሃይል አማራጭ ሃይላቸው ከ750 ዋት የበለጠ ነገር ግን ከ75 ኪ.ዋት ያልበለጠ ለመስኖ የሚያገለግሉ ሞተሮች |
| 35 | 8501.5330 | ውሃ ከጥልቅ ጉድጓድ ወይም ከዎንዞች ወይም ከኩሬ ወይም ከግድብ ወደማሳ ለመግፋት የሃይል አማራጭ ሃይላቸው ከ75 ኪ.ዋት የበለጠ ለመስኖ የሚያገለግሉ ሞተሮች |
| 36 | 8501.6130 | ውሃ ከጥልቅ ጉድጓድ ወይም ከዎንዞች ወይም ከኩሬ ወይም ከግድብ ወደማሳ ለመግፋት የሃይል አማራጭ ሃይላቸው ከ75 ኬ.ቪ.ኤ ያልበለጠ ለመስኖ የሚያገለግሉ ጀነሬተሮች፣ ለኮሜርሻል አኳካልቸር እና ለዓሣ ማዘጋጃ እና ማቀነባበሪያ የሚውል ባለ 3 ፌዝ ጀነሬተር |
| 37 | 8501.6230 | ውሃ ከጥልቅ ጉድጓድ ወይም ከዎንዞች ወይም ከኩሬ ወይም ከግድብ ወደማሳ ለመግፋት የሃይል አማራጭ ሃይላቸው ከ75 ኬ.ቪ.ኤ የበለጠ ነገር ግን ከ375 ኬ.ቪ.ኤ ያልበለጠ ለመስኖ የሚያገለግሉ ጀነሬተሮች |
| 38 | 8501.6330 | ውሃ ከጥልቅ ጉድጓድ ወይም ከዎንዞች ወይም ከኩሬ ወይም ከግድብ ወደማሳ ለመግፋት የሃይል አማራጭ ሃይላቸው ከ375 ኬ.ቪ.ኤ የበለጠ ነገር ግን ከ750 ኬ.ቪ.ኤ ያልበለጠ ለመስኖ የሚያገለግሉ ጀነሬተሮች |
| 39 | 8501.6430 | ውሃ ከጥልቅ ጉድጓድ ወይም ከዎንዞች ወይም ከኩሬ ወይም ከግድብ ወደማሳ ለመግፋት የሃይል አማራጭ ሃይላቸው ከ750 ኬ.ቪ.ኤ የበለጠ ለመስኖ የሚያገለግሉ ጀነሬተሮች |
| 40 | 8502.1100 | ውሃ ከጥልቅ ጉድጓድ ወይም ከዎንዞች ወይም ከኩሬ ወይም ከግድብ ወደማሳ ለመግፋት የሃይል አማራጭ ሃይላቸው ከ75 ኬ.ቪ.ኤ ያልበለጠ ለመስኖ የሚያገለግሉ ጀነሬተሮች |
| 41 | 8502.1200 | ውሃ ከጥልቅ ጉድጓድ ወይም ከወንዞች ወይም ከኩሬ ወይም ከግድብ ወደማሳ ለመግፋት የሃይል አማራጭ ሃይላቸው ከ75 ኬ.ቪ.ኤ የበለጠ ነገር ግን ከ375 ኬ.ቪ.ኤ ያልበለጠ ለመስኖ የሚያገለግሉ ጀነሬተሮች |
| 42 | 8502.1300 | ውሃ ከጥልቅ ጉድጓድ ወይም ከዎንዞች ወይም ከኩሬ ወይም ከግድብ ወደማሳ ለመግፋት የሃይል አማራጭ ሃይላቸው ከ375 ኬ.ቪ.ኤ የበለጠ ለመስኖ የሚያገለግሉ ጀነሬተሮች |
| 43 | 8502.3100 | ውሃ ከጥልቅ ጉድጓድ ወይም ከዎንዞች ወይም ከኩሬ ወይም ከግድብ ወደማሳ ለመግፋት የሃይል አማራጭ፣ ለመስኖ የሚያገለግሉ የኤሌክትሪክ ሃይል አመንጪ ሙሉ ክፍሎች በነፋስ ሃይል የሚሰሩ |
| 44 | 8502.3900 | ውሃ ከጥልቅ ጉድጓድ ወይም ከዎንዞች ወይም ከኩሬ ወይም ከግድብ ወደማሳ ለመግፋት የሃይል አማራጭ፣ ለመስኖ የሚያገለግሉ የኤሌክትሪክ ሃይል አመንጪ ሙሉ ክፍሎች |



ስልክ
251-11-155 24 00,22 66 98
251-11-155 00 81,83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ
P.O.Box 1905,1037
አባክዎን መልስ ሲፅፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ
ፋክስ/Fax
251-11-156 01 24,55 14 96
251-11-155 11 38
MoF_Ethiopia
facebook.com/MoFEDet
mofed.gov.et

| ተ.ቁ | ታሪፍ ቁጥር | የዕቃው ዓይነት |
|---|---|---|
| 45 | 8502.4000 | ውሃ ከጥልቅ ጉድጓድ ወይም ከወንዞች ወይም ከኩሬ ወይም ከግድብ ወደማሳ ለመግፋት የሃይል አማራጭ ለመስኖ የሚያገለግሉ የኤሌክትሪክ ሮተሪ ኮንቨርተሮች |
| 46 | 8704.2213 | የወተት ማጓጓዣ ማቀዝቀዣ የተገጠመለት ተሽከርካሪ፣ ህይወት ያላቸውን ዶሮዎች ለማጓጓዝ የሚውሉ በልዩ ሁኔታ የተዘጋጁ የጭነት መኪና፣ ተንቀሳቃሽ ወርክሾ እና ጋራጅ አዲስ፣ የሆርቲካልቸር፣ ፍሎሪካልቸር፣ የእንስሳት ምርት እና ተዋፅዖ እና ዓሳ ምርት ማጓጓዣ ቀዝቃዛ ተሽከርካሪ (ፍሪጅ የተገጠመበት)፣ ሽፍን የዓሣ ማጓጓዣ ተሽከርካሪዎች፣ ማቀዝቀዣ ያላቸው የዓሣ ማጓጓዣ ተሽከርካሪዎች፣ የቁም እንስሳት ማጓጓዣ ተሽከርካሪዎች |
| 47 | 8716.2020 | ለእርሻ አገልግሎት የሚውሉ እራሳቸው ላይ የሚጭኑ ወይም ከራሳቸው ላይ እቃዎችን የሚያወርዱ እና ከፊል ተጎታች የሆኑ ጋሪዎች አዲስ |
| 48 | 8903.9200 | የዓሣ ማጥመጃ እና መሰብሰቢያ ጀልባ (ከውስጥ ሞተሩ የተገጠመ) |
| 49 | 9013.8000 | አጉሊ መነፅር፣ በራስ ላይ የሚጠለቅ አጉሊ መነፅር ከኤልኢዲ ብርሃን ጋር፣ የጠረጴዛ ላይ አጉሊ መነፅር ከፍሎረሰንት አምፖል ጋር |
| 50 | 9026.1000 | የመስኖ መሠረተ ልማት ጥናት፣ ዲዛይንና ግንባታ ቁጥጥር የሚወሉ፣ የመስኖ ውሃ አጠቃቀም ስርዓትን በመስኖ አውታሮች ለመተግበር የፈሳሽ፡- የውሃ ልክ፣ የግፊት መጠን ወይም ሌሎች ቫሪብሎች የሚለኩ ወይም የሚፈትሹ ኢንስትሩሜንትና መሳሪያዎች፡- ለምሳሌ ሌቪል ጌጆች፣ ማኖሜትሮች፣ ሂት ሜትሮች ወይም መፈተሻዎች፣ ለመስኖ ውሃ መጠን መቆጣጠሪያና መፈተሻ የሚውሉ |

**በሠንጠረዥ 2 ሥር ከቀረጥና ታክስ ነፃ የተፈቀዱት እቃዎች ተግባራዊ ሲደረግ ግብርና ሚኒስቴር፡-**

1. እነዚህ እቃዎች በተፈቀደው መብት ወደአገር ሲገቡ ለህዝብ ይፋ በሚሆን ግልጽ መስፈርት በግብርና ሚኒስቴር ፈቃድና ቁጥጥር ሥር እንዲያስገቡ ወይም ሚኒስቴሩ ፍቃድ በሰጣቸው አካላት በኩል እንዲገቡ እንዲደረግ፣
2. እቃዎቹ ለታለመለት ዓላማ መዋላቸውን ግብርና ሚኒስቴር ክትትልና ቁጥጥር እንዲያደርግ አፈጻጸሙንም በየስድስት ወሩ በእያንዳንዱ



ስልክ 251-11-155 24 00,22 66 98 251-11-155 00 81,83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ P.O.Box 1905,1037 እባክዎን መልስ ሲፅፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ
ፋክስ/Fax 251-11-156 01 24,55 14 96 251-11-155 11 38
MoF_Ethiopia facebook.com/MoFEDet mofed.gov.et

የተፈቀደ የግብርና ግብአት በአገር ውስጥ ያለው ፍላጎትና ክፍተት፣ የገባ ግብአት መጠንና ክፍተቱ የደረሰበት ደረጃ እና በግብርናው ዘርፍ በዚህ ማበረታቻ ሊገኝ የታሰበው ውጤትና አፈጻጸሙን ያካተተ ሪፖርት ለገንዘብ ሚኒስቴር እንዲያቀርብ፣

3. እቃዎቹ ለአርሶ/አርብቶ አደሩ ወይም ለተጠቃሚው ሲደርሱ የተሸጡበትን ዋጋ በየሦስት ወሩ ለገንዘብ ሚኒስቴር ሪፖርት እንዲያቀርብ፣

4. ይህ የቀረጥና ታክስ ማበረታቻ በግብርናው ዘርፍ ምርትና ምርታማነት ላይ ያስከተለውን ውጤት (Impact Assesement) በጥናት በየዓመቱ ለገንዘብ ሚኒስቴር ሪፖርት እንዲያቀርብ፣

1.3. ከታች በሠንጠረዥ 3 የቀረቡት እቃዎች በአገር ውስጥ በሚገኙ ኢንዱስትሪዎች በመመረት ላይ ያሉና መመረት የሚችሉ ናቸው። ስለዚህ ግብርናው ከኢንዱስትሪው ጋር እንዲተሳሰርና ዘርፎቹ እርስ በእርስ እንዲመጋገቡ ለማስቻል ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እና ግብርና ሚኒስቴር እቃዎቹ በአገር ውስጥ ተመርተው ለግብርናው መቅረብ ስለሚችሉበት ሁኔታ በጋራ እንዲሰሩ፤ እነዚህ በአገር ውስጥ የሚመረቱ እቃዎች ለግብርናው ዘርፍ በዝቅተኛ ዋጋ እንዲደርሱ ለማስቻል ለግብርና ዓላማ ከአገር ውስጥ ምርት ግብይት ሲፈፀምባቸው በአዋጅ ቁጥር 285/2002 አንቀጽ 8 (4) ለገንዘብ ሚኒስቴር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ እንዲሆኑ፤

**ሠንጠረዥ 3፡ ከአገር ውስጥ ምርት ግብይት ሲፈፀምባቸው ከተጨማሪ እሴት ታክስ፣ ተርን ኦቨር ታክስ እና ኤክሳይዝ ታክስ ነጻ የተደረጉ ዕቃዎች**

| ተ.ቁ | ታሪፍ ቁጥር | የዕቃው ዓይነት |
|---|---|---|
| 1 | 3920.9990 | የተቀነባበረ ወተት ማሸጊያ ፕላስቲኮች |
| 2 | 3923.1000 | ፕላስቲክ የተለያዩ መጠን ያለው የማር መያዣ ፉድ ግሬድድ፣ ከፕላስቲክ |



ስልክ
251-11-155 24 00,22 66 98
251-11-155 00 81,83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ
P.O.Box 1905,1037
እባክዎን መልስ ሲፅፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ
ፋክስ/Fax
251-11-156 01 24,55 14 96
251-11-155 11 38
MoF_Ethiopia
facebook.com/MoFEDet
mofed.gov.et

ቁጥር
Ref. No
ቀን
Date.

| ተ.ቁ | ታሪፍ ቁጥር | የዕቃው ዓይነት |
|---|---|---|
| | | የተሰራ የዶሮ እንቁላል መጣያ ሳጥን ወይም ጎጆ፣ ከፕላስቲክ የተሰራ የዶሮ እንቁላል መያዣና ማከማቻ ሳህን፣ ከፕላስቲክ የተሰራ የዶሮ ጫጩት መያዣ፣ ማከማቻና ማጓጓዣ ሳጥን፣ ከፕላስቲክ የተሰራ ቄብና ኩክኔ የዶሮ መያዣ፣ ማከማቻና ማጓጓዣ ሳጥን |
| 3 | 3925.1000 | የዓሣ ማራቢያ ታንከሮች፣ አውቶማቲክ ያልሆነ ዶሮ መመገቢያ ከፕላሰቲክ የተሰራ፣ አውቶማቲክ ያልሆነ ዶሮ ውኃ ማጠጫ ከፕላሰቲክ የተሰራ |
| 4 | 3925.9000 | የዓሣ ማራቢያ ታንከሮች |
| 5 | 3926.9090 | ፕላስቲክ እናት ንብ መያዣ፣ የዓሣ ማጥመጃ መረቦች መስሪያ መርፌ፣ ፕላስቲክ ከቀፎ ውስጥና ውጪ ንቦችን መመገቢያ፣ ፕላስቲክ ፍሎ የንብ ቀፎ ፍሬም፣ ፕላስቲክ ሰው-ሠራሽ የሰም እንጀራ፣ ፕላስቲክ እጭ ማጋቢያ መርፌ፣ ፕላስቲክ የእናት ንብ ማቆያ፣ ፕላስቲክ የእናት ንብ ማግለያ፣ ፕላስቲክ የእናት ንብ ነቁር (ሴል)፣ ፕላስቲክ የእናት ንብ ነቁር መያዣ፣ የጽጌ ብናኝ ማጥመጃ፣ ፕላስቲክ ሙጫ መሰብሰቢያ |
| 6 | 4421.9990 | አውቶማቲክ ፍሎ የንብ ቀፎ |
| 7 | 4819.3000 | የዓሣ መኖ ማሸጊያ ከረጢት |
| 8 | 6203.1200 | ለንብ ማነቢያ አገልግሎት የሚውል ቱታ |
| 9 | 6203.1900 | ለንብ ማነቢያ አገልግሎት የሚውል ቱታ |
| 10 | 6203.3200 | የንብ መነደፍን መከላከያ ጃኬት |
| 11 | 6203.3300 | የንብ መነደፍን መከላከያ ጃኬት |
| 12 | 6203.3900 | የንብ መነደፍን መከላከያ ጃኬት |
| 13 | 6214.9000 | የንብ መነደፍን መከላከያ ዓይነርግብ (ግማሽ ጨርቅ) |
| 14 | 6305.1000 | የሰብል እና መኖ ምርት ማከማቻ ጆኒያ |
| 15 | 6305.3300 | የሰብል ምርት ማከማቻ ፒ. ፒ. (ሄርማቲክ) ጆኒያ |
| 16 | 7010.9000 | የተለያዩ መጠን ያለው የማር መያዣ ብርጭቆ ፉድ ግሬድድ |
| 17 | 7210.1100 | ጋልቫነይዝድ ሽት ሜታል ከ0.5 ሚሚ እና በላይ ውፍረት ለምርት ማከማቻ ጎተራ መስሪያ የሚያገለግል |
| 18 | 7223.0000 | የፍሬም ሽቦ ውፍረቱ 4 ሚሜ የሆነ |



ስልክ 251-11-155 24 00,22 66 98 251-11-155 00 81,83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ P.O.Box 1905,1037 እባክዎን መልስ ሲፅፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ
ፋክስ/Fax 251-11-156 01 24,55 14 96 251-11-155 11 38
MoF_Ethiopia
facebook.com/MoFEDet
mofed.gov.et

ቁጥር
Ref. No
ቀን
Date.

| ተ.ቁ | ታሪፍ ቁጥር | የዕቃው ዓይነት |
|---|---|---|
| 19 | 7303.0000 | ለመስኖ ውሃ ማስተላለፊያ አገልግሎት የሚውሉ ቱቦዎች፣ ቧንቧዎች እና ውስጠ ክፍት ፕሮፋይልስ፣ ከቀለጠ ብረት የተሠሩ |
| 20 | 7304.3100 | ለመስኖ ውሃ ማስተላለፊያ አገልግሎት የሚውሉ ቱቦዎች፣ ቧንቧዎች እና ውስጠ ክፍት ፕሮፋይልስ፣ ብየዳ የሌላቸው ከብረት/ከቀለጠ ብረት ወይም ከዐረብ ብረት የተሠሩ:- ክብ ክሮሴክሽን ያላቸው፣ ከብረት ወይም አሎይ ካልሆነ የዐረብ ብረት የተሰሩ--በመለስተኛ ሙቀት የተሳቡ ወይም በመለስተኛ ሙቀት የተዳመጡ/በመለስተኛ ሙቀት ተለይተው የወጡ/ ለመስኖ ጥልቅ ጉድጓዶች ቁፋሮ፣ ሽፋን፣ ውሃ ማውጫ እና ማስተላለፊያ የሚያገለግሉ |
| 21 | 7304.3900 | ለመስኖ ውሃ ማስተላለፊያ አገልግሎት የሚውሉ ቱቦዎች፣ ቧንቧዎች እና ውስጠ ክፍት ፕሮፋይልስ፣ ብየዳ የሌላቸው ከብረት/ከቀለጠ ብረት ወይም ከዐረብ ብረት የተሠሩ :-ሌሎች፣ ክብ ክሮሴክሽን ያላቸው፣ ከብረት ወይም አሎይ ካልሆነ የዐረብ ብረት የተሰሩ፤ ለመስኖ ጥልቅ ጉድጓዶች ቁፋሮ፣ ሽፋን፣ ውሃ ማውጫ እና ማስተላለፊያ የሚያገለግሉ |
| 22 | 7304.4100 | ለመስኖ ውሃ ማስተላለፊያ አገልግሎት የሚውሉ ሌሎች፣ ክብ ክሮሴክሽን ያላቸው፣ ከማይዝግ የዐረብ ብረት የተሰሩ-- በመለስተኛ ሙቀት የተሳቡ ወይም በመለስተኛ ሙቀት የተዳመጡ/በመለስተኛ ሙቀት ተለይተው የወጡ/ ለመስኖ ጥልቅ ጉድጓዶች ቁፋሮ፣ ሽፋን፣ ውሃ ማውጫ እና ማስተላለፊያ የሚያገለግሉ |
| 23 | 7304.4900 | ለመስኖ ውሃ ማስተላለፊያ አገልግሎት የሚውሉ ሌሎች፣ ክብ ክሮሴክሽን ያላቸው፣ ከማይዝግ የዐረብ ብረት የተሰሩ-- ሌሎች ቧንቧዎች እና ቱቦዎች |
| 24 | 7304.5100 | ለመስኖ ውሃ ማስተላለፊያ አገልግሎት የሚውሉ ሌሎች፣ ክብ ክሮሴክሽን ያላቸው፣ ከሌሎች የዐረብ ብረት አሎይ የተሰሩ-- በመለስተኛ ሙቀት የተሳቡ ወይም በመለስተኛ ሙቀት የተዳመጡ/በመለስተኛ ሙቀት ተለይተው የወጡ/ ለመስኖ ጥልቅ ጉድጓዶች ቁፋሮ፣ ሽፋን፣ ውሃ ማውጫ እና ማስተላለፊያ የሚያገለግሉ |
| 25 | 7304.5900 | ለመስኖ ውሃ ማስተላለፊያ አገልግሎት የሚውሉ ሌሎች፣ ክብ ክሮሴክሽን |



ስልክ
251-11-155 24 00,22 66 98
251-11-155 00 81,83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ
P.O.Box 1905,1037
አባክዎን መልስ ሲፅፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ
ፋክስ/Fax
251-11-156 01 24,55 14 96
251-11-155 11 38
MoF_Ethiopia
facebook.com/MoFEDet
mofed.gov.et

ቁጥር
Ref. No
ቀን
Date

| ተ.ቁ | ታሪፍ ቁጥር | የዕቃው ዓይነት |
|---|---|---|
| | | ያላቸው፣ ከሌሎች የዐረብ ብረት አሎይ የተሰሩ - ሌሎች ቧንቧዎች እና ቱቦዎች |
| 26 | 7304.9000 | ለመስኖ ውሃ ማስተላለፊያ አገልግሎት የሚውሉ ሌሎች፣ ክብ ክሮሴክሽን ያላቸው፣ ከማይዝግ የዐረብ ብረት የተሰሩ - ሌሎች ቧንቧዎች እና ቱቦዎች ለመስኖ ጥልቅ ጉድጓዶች ቁፋሮ፣ ሽፋን፣ ውሃ ማውጫ እና ማስተላለፊያ የሚያገለግሉ |
| 27 | 7306.3000 | ለመስኖ ውሃ ማስተላለፊያ አገልግሎት የሚውሉ ሌሎች፣ የተበየዱ ክብ ክሮሴክሽን ያላቸውና ከብረት ወይም አሎይ ካልሆኑ የዐረብ ብረት የተሰሩ ለመስኖ ጥልቅ ጉድጓዶች ቁፋሮ፣ ሽፋን፣ ውሃ ማውጫ እና ማስተላለፊያ የሚያገለግሉ |
| 28 | 7306.4000 | ለመስኖ ውሃ ማስተላለፊያ አገልግሎት የሚውሉ ሌሎች፣የተበየዱ ክብ ክሮሴክሽን ያላቸው ከማይዝግ የዐረብ ብረት የተሰሩ ለመስኖ ጥልቅ ጉድጓዶች ቁፋሮ፣ ሽፋን፣ ውሃ ማውጫ እና ማስተላለፊያ የሚያገለግሉ |
| 29 | 7306.5000 | ለመስኖ ውሃ ማስተላለፊያ አገልግሎት የሚውሉ ሌሎች፣ የተበየዱ ክብ ክሮሴክሽን ያላቸው ከሌሎች የዐረብ ብረት አሎይ የተሰሩ ለመስኖ ጥልቅ ጉድጓዶች ቁፋሮ፣ ሽፋን፣ ውሃ ማውጫ እና ማስተላለፊያ የሚያገለግሉ |
| 30 | 7307.1100 | ለመስኖ ውሃ ማስተላለፊያ አገልግሎት የሚውሉ የቱቦዎች ወይም የቧንቧዎች ማገጣጠሚያዎች /ለምሳሌ ማንኛውም ማገናኛዎች፣ ኤልቦዎች፣ ስሊቮች/ከብረት ወይም ከዐረብ ብረት የተሠሩ፣ በማቅለጥ የተሰሩ መገጣጠሚያዎች፣ በቅጥቀጣ ወይም በመዳመጥ ቅርፅ ሊሰጠው ከማይችል የቀለጠ ብረት የተሠሩ ለመስኖ ስራ የሚያገለግሉ |
| 31 | 7307.1900 | ለመስኖ ውሃ ማስተላለፊያ አገልግሎት የሚውሉ የቱቦዎች ወይም የቧንቧዎች ማገጣጠሚያዎች /ለምሳሌ ማንኛውም ማገናኛዎች፣ ኤልቦዎች፣ ስሊቮች/ከብረት ወይም ከዐረብ ብረት የተሠሩ-በማቅለጥ የተሰሩ መገጣጠሚያዎች፡- ለመስኖ ስራ የሚያገለግሉ |
| 32 | 7307.2100 | ለመስኖ ውሃ ማስተላለፊያ አገልግሎት የሚውሉ ሌሎች ከማይዝግ የዐረብ |



ስልክ
251-11-155 24 00,22 66 98
251-11-155 00 81,83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ
P.O.Box 1905,1037
እባክዎን መልስ ሲፅፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ
ፋክስ/Fax
251-11-156 01 24,55 14 96
251-11-155 11 38
MoF_Ethiopia
facebook.com/MoFEDet
mofed.gov.et

ቁጥር ____________
Ref. No
ቀን ____________
Date.

| ተ.ቁ | ታሪፍ ቁጥር | የዕቃው ዓይነት |
|---|---|---|
| | | ብረት የተሰሩ ፍላንጆች ለመስኖ ስራ የሚያገለግሉ |
| 33 | 7307.2200 | ለመስኖ ውሃ ማስተላለፊያ አገልግሎት የሚውሉ ሌሎች ከማይዝግ የዐረብ ብረት የተሰሩ ጥርስ የወጣላቸው ኤልቦዎች፣ ማጠፊያዎች እና ስሊቮች |
| 34 | 7307.2300 | ለመስኖ ውሃ ማስተላለፊያ አገልግሎት የሚውሉ ሌሎች ከማይዝግ የዐረብ ብረት የተሰሩ- ጫፍ ለጫፍ በመቀጣጠል ወይም ጎን ለጎን በማጣበቅ የተበየዱ ማገጣጠሚያዎች |
| 35 | 7307.2900 | ለመስኖ ውሃ ማስተላለፊያ አገልግሎት የሚውሉ ሌሎች ከማይዝግ የዐረብ ብረት የተሰሩ- ሌሎች የተለያዩ የመስኖ ማስተላለፊያ ቧንቧ መስመሮች መገጣጠሚያ |
| 36 | 7307.9100 | ለመስኖ ውሃ ማስተላለፊያ አገልግሎት የሚውሉ ሌሎች የቱቦዎች ወይም የቧንቧዎች ማገጣጠሚያዎች/ለምሳሌ ማንኛውም ማገናኛዎች፣ኤልቦዎች፣ ስሊቮች/ ከብረት ወይም ከዐረብ ብረት የተሠሩ - ፍላንጆች ለመስኖ ስራ የሚያገለግሉ |
| 37 | 7307.9200 | ለመስኖ ውሃ ማስተላለፊያ አገልግሎት የሚውሉ ሌሎች የቱቦዎች ወይም የቧንቧዎች ማገጣጠሚያዎች /ለምሳሌ ማንኛውም ማገናኛዎች፣ኤልቦዎች፣ ስሊቮች/ ከብረት ወይም ከዐረብ ብረት የተሠሩ- ጥርስ የወጣላቸው ኤልቦዎች፣ ማጠፊያዎች እና ስሊቮች ለመስኖ ስራ የሚያገለግሉ |
| 38 | 7307.9300 | ለመስኖ ውሃ ማስተላለፊያ አገልግሎት የሚውሉ ሌሎች የቱቦዎች ወይም የቧንቧዎች ማገጣጠሚያዎች /ለምሳሌ ማንኛውም ማገናኛዎች፣ኤልቦዎች፣ ስሊቮች/ከብረት ወይም ከዐረብ ብረት የተሠሩ- ጫፍ ለጫፍ በመቀጣጠል ወይም ጎን ለጎን በማጣበቅ የተበየዱ ማገጣጠሚያዎች ለመስኖ ስራ የሚያገለግሉ |
| 39 | 7307.9900 | ለመስኖ ውሃ ማስተላለፊያ አገልግሎት የሚውሉ የቱቦዎች ወይም የቧንቧዎች ማገጣጠሚያዎች /ለምሳሌ ማንኛውም ማገናኛዎች፣ ኤልቦዎች፣ ስሊቮች/ከብረት ወይም ከዐረብ ብረት የተሠሩ- ሌሎች ለመስኖ ስራ የሚያገለግሉ |
| 40 | 7308.9000 | አውቶማቲክ ያልሆነ ለዶሮ እርባታ የሚያገለግል ኬጆች |



ስልክ
251-11-155 24 00,22 66 98
251-11-155 00 81,83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ
P.O.Box 1905,1037
አባክዎን መልስ ሲፅፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ
ፋክስ/Fax
251-11-156 01 24,55 14 96
251-11-155 11 38
MoF_Ethiopia
facebook.com/MoFEDet
mofed.gov.et

ቁጥር ________
Ref. No
ቀን ________
Date.

| ተ.ቁ | ታሪፍ ቁጥር | የዕቃው ዓይነት |
|---|---|---|
| 41 | 7310.2900 | የወተት ማለቢያ፣ መያዣና ማጓጓዣ እቃዎችና ባልዲዎች፣ የተለያዩ መጠን ያለው የማር መያዣ ፉድ ግሬድድ (ስቴንለስ ስቲል) |
| 42 | 8007.0000 | ጭስ ማጨሻ |
| 43 | 8201.1000 | የጽጌ ብናኝ ማፈሻ አካፋ፣ የእናት ንብ ማግለያ ማፅጃ አካፋ |
| 44 | 8205.5900 | የቀፎ መክፈቻ መሮ |
| 45 | 8208.4000 | የማር ሽፋን መግለጫ ቢላዋ |
| 46 | 8215.9900 | የማር ሽፋን መግለጫ ሹካ |
| 47 | 8413.2000 | ለመስኖ የሚውሉ የእጅ ፓምፖች፣ በንዑስ አንቀጽ 8413.11 ወይም 8413.19 ከሚመደቡት ሌላ ለመስኖ አገልግሎት የሚውሉ |
| 48 | 8414.3000 | ኮምፕሬሰር |
| 49 | 8418.1020 | የሆርቲካልቸር፣ ፍሎሪካልቸር፣ የእንስሳት ምርት እና ተዋፅዖ እና ዓሳ ምርት እና የእንስሳት ክትባት ማከማቻ ቀዝቃዛ መጋዘን፣ |
| 50 | 8418.3020 | የዓሣ ማቀዝቀዣ የአግዳሚ ዲፕ ፈሪዘሮች |
| 51 | 8418.6120 | የወተት ማቀዝቀዣ እቃዎች |
| 52 | 8418.6920 | ቺሊንግ ታንክ፣ ለዓሣ ማቆያ የበረዶ የሚያመርት ማሽን፣ ሌሎች የዓሣ ፈጣን ማቀዝቀዣዎች እና ቺለሮች |
| 53 | 8418.9100 | የሪፍሪጀሬተር ወይም የማቀዝቀዣ መሳሪያዎችን ለማስቀመጥ የተሰሩ ዕቃዎች |
| 54 | 8418.9900 | የዓሣ ማቀዝቀዣ፣ ማከማቻ |
| 55 | 8716.3120 | በትራክተር የሚጎተት ለነዳጅ፤ ለሞላሰስና ለውሃ ማመላለሻ ሚገለግሉ ቦቴዎች/ የውሃ አዲስ |
| 56 | 8716.3920 | ለእርሻ አገልግሎት የሚውሉ ተጎታች ጋሪዎች |
| 57 | 9031.2000 | የናሙና መስሪያ ጠረጴዛ |
| 58 | 9603.1000 | ባለእጀታ የንብ ብሩሽ |
| 59 | 9604.0000 | የማር ማጣሪያ ወንፊት፣ ነጠላ/ድርብ ወንፊት |



ስልክ
251-11-155 24 00,22 66 98
251-11-155 00 81,83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ
P.O.Box 1905,1037
እባክዎን መልስ ሲፅፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ
ፋክስ/Fax
251-11-156 01 24,55 14 96
251-11-155 11 38
MoF_Ethiopia
facebook.com/MoFEDet
mofed.gov.et

ከላይ በሠንጠረዥ 1፣ 2 እና 3 የተመለከቱት የግብርና እቃዎች፣ መሣሪያዎች እና ግብዓቶች ለግብርና ዓላማ ተብለው ከአገር ውስጥ ምርት ግብይት ሲፈጸምባቸው ከታክስ ነፃ የሚሆኑት ከተጨማሪ እሴት ታክስ፣ ከተርን ኦቨር ታክስ እና ከኤክሳይዝ ታክስ ሲሆን፣ ለሥራ አመቺነት ሲባል ታክሱን ግብይቱ በሚፈጸምበት ወቅት በመክፈል ለግብርና ዓላማ መዋላቸው በግብርና ሚኒስቴር ማረጋገጫ ሲቀርብ ተመላሽ ሥርዓት የሚፈጸም መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ይህ ማበረታቻ ውጤታማ ይሆን ዘንድ ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እና ግብርና ሚኒስቴር በቅንጅት በመስራት አገር ውስጥ የሚመረቱ ምርቶች ለግብርናው ዘርፍ በበቂ ሁኔታ እየቀረቡ ስለመሆናቸው ክትትል እንዲያደርጉና ግብርናው ከኢንዱስትው ጋር ትስስር እንዲያደርግ የሚጠበቅ ሲሆን፤ ግብርና ሚኒስቴርም ለግብርናው ዘርፍ የሚያስፈልጉ ግብአቶች በአገር ውስጥ እንዲመረቱ የሚፈለገውን መጠን፣ ቴክኖሎጂ፣ ዲዛይን፣ ወዘተ ለሚመለከተው ተቋም እንዲያቀርብ፤ ተቋሙም የሚፈለጉ ምርቶች እንዲመረቱ ኢንዱስትሪዎችን እንዲያመርቱ እንዲያደርጉ እና ለአምራቾቹ የሚያስፈልግ ማበረታቻ ሲኖር ለገንዘብ ሚኒስቴር ማቅረብ የሚቻል ሲሆን በአገር ውስጥ ሙሉ በሙሉ ወይም በበቂ ሁኔታ የማይገኙ ከሆነም ለገንዘብ ሚኒስቴር እንዲያሳውቁ እንጠይቃለን፡፡

2. የሚከተሉት የምግብ ዘይት ለማምረት የሚውሉ ግብዓቶች ነሀሴ 28 ቀን 2013 ዓ.ም በቁጥር ማኢ30/7/1431 የተላለፈው ፖሊሲ ሥራ ላይ እስካለ ድረስ የምግብ ዘይት አምራቾች ለግብዓትነት ሲያስመጧቸው የኢንዱስትሪዎቹ ንግድ እና ኢንቨስትመንት ፈቃድ እየተረጋገጠ በሚከተለው ታሪፍ መጣኔ እንዲስተናገዱ፤

| ተ.ቁ | ጉምሩክ ታሪፍ ቁጥር | ታሪፍ መጣኔ |
|---|---|---|
| 1 | 1507.1000 | ነፃ |
| 2 | 1508.1000 | ነፃ |
| 3 | 1511.1000 | ነፃ |
| 4 | 1512.1100 | ነፃ |



ስልክ
251-11-155 24 00,22 66 98
251-11-155 00 81,83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ
P.O.Box 1905,1037
አባክዎን መልስ ሲፅፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ
ፋክስ/Fax
251-11-156 01 24,55 14 96
251-11-155 11 38
MoF_Ethiopia
facebook.com/MoFEDet
mofed.gov.et

ቁጥር
Ref. No
ቀን
Date.

| ተ.ቁ | ጉምሩክ ታሪፍ ቁጥር | ታሪፍ መጣኔ |
|---|---|---|
| 5 | 1512.2100 | ነፃ |
| 6 | 1513.1100 | ነፃ |
| 7 | 1513.2100 | ነፃ |
| 8 | 1514.1100 | ነፃ |
| 9 | 1514.9100 | ነፃ |
| 10 | 1515.1100 | ነፃ |
| 11 | 1515.2100 | ነፃ |
| 12 | 2809.2000 | ነፃ |
| 13 | 2918.1400 | ነፃ |
| 14 | 3204.9000 | ነፃ |
| 15 | 3802.9000 | ነፃ |
| 16 | 3901.1000 | ነፃ |
| 17 | 3901.2000 | ነፃ |
| 18 | 3902.1000 | ነፃ |
| 19 | 3907.2000 | ነፃ |
| 20 | 3907.6100 | ነፃ |

3. ታሪፍ አንቀጽ 87.03 ተጨማሪ ማሻሻያ በገንዘብ ሚኒስቴር እስከሚገለጽ ድረስ የታሪፍ አመዳደቡ፣ የጉምሩክ ታሪፍ መጣኔው፣ ኤክሳይስ ታክስ መጣኔው፣ ተጨማሪ እሴት ታክስ መጣኔው እና ሱር ታክስ መጣኔው ሀምሌ 05 ቀን 2011 ዓ.ም በቁጥር ማኢ/30/47/1 በተጻፈ ደብዳቤ ሥራ ላይ በዋለው 2017 ቨርሽን የሀርሞናይዝድ ሲስተም የጉምሩክ ታሪፍ ማሻሻያ ቁጥር 8 መሠረት እንዲፈጸም፤

4. በምዕራፍ 58 ላይ ተመድበው 25 በመቶ የጉምሩክ ታሪፍ የተጣለባቸው ታሪፍ ቁጥሮች ከሱር ታክስ ነፃ ናቸው።



ስልክ
251-11-155 24 00,22 66 98
251-11-155 00 81,83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ
P.O.Box 1905,1037
አባክዎን መልስ ሲፅፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ
ፋክስ/Fax
251-11-156 01 24,55 14 96
251-11-155 11 38
MoF_Ethiopia
facebook.com/MoFEDet
mofed.gov.et

ቁጥር ______
Ref. No
ቀን ______
Date.

ስለሆነም ሀምሌ 28 ቀን 2013 ዓ.ም በቁጥር ማኢ30/7/1141 በተጻፈ ደብዳቤ ላይ የተገለጹት ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው ከደብዳቤው ጋር ተያይዞ ተልኮ የነበረው ማሻሻያ በዚህ አባሪ በተደረገው አማርኛና እንግሊዘኛ ቅጂ እያንዳንዱ 372 ገጽ 2 ጥራዝ የጉምሩክ ታሪፍ ማሻሻያ ተተክቷል፡፡

ከሠላምታ ጋር

እዮብ ተካልኝ (ዶ/ር)
ሚኒስትር ዴኤታ

**ግልባጭ፡-**

- ለታክስ ፖሊሲ ዳይሬክቶሬት
  ገንዘብ ሚኒስቴር
- ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
- ለግብርና ሚኒስቴር (ያለአባሪ)
  አዲስ አበባ



ስልክ 251-11-155 24 00,22 66 98 / 251-11-155 00 81,83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ P.O.Box 1905,1037
እባክዎን መልስ ሲፅፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ
ፋክስ/Fax 251-11-156 01 24,55 14 96 / 251-11-155 11 38
MoF_Ethiopia
facebook.com/MoFEDet
mofed.gov.et